## አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 8ኛ ክፍል

የተማሪው ስም : ___________________________________ስልክ ቁጥር: _____________________
የአስተማሪው ስም: ___________________________________ቀን : _________________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

<u>**አቅጣጫዎች:**</u> እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **8.1 ተማሪው የሰው ልጅ እድገት ደረጃዎችን ከራሱ እድገት ደረጃ ጋር ያገናዝባል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪው ሰዎች ዕድሚያቸው ሲጨምር አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና፣ ስሜታዊ ለውጥ እነደሚኖራቸው ይገነዘባል። አካላዊ ዕድገትና የአካል ክፍሎች ጥናት ይዳሰሳሉ። ተማሪው ራሱን የማወቅ እና የመቀበል ሁኔታውን ለመጨመር የተማሪው ነባራዊ የዕድገት ደረጃ ጋር በማያያዝ የ ሰው ልጅ አካላዊና አዕምሮአዊ የዕድገት ደረጃዎች ይታያሉ። ከሰው ልጅ ዕድገት ጋር የሚያያዙ ተቀባይነት ያላቸው ፅንሰ-ሃሳቦች ይቀርባሉ።

___ **8.2 ተማሪው ስነ ወሲባዊ ዕድገትን የ ማንነት አንድ አካል እነደሆነ ይለያሉ።**
<u>መግለጫ</u>: ዋናው የሚዳሰሰው ፅንሰ ሃሳብ የራስን ስነ ወሲባዊ ማንነት ዕድገት ስለማወቅ ነው።

___ **8.3 ተማሪው ከውሳኔ በፊት ማድረግ ስለሚገባው ጥልቅ የሆነ ማመዛዘን እና እነዴት ውሳኔው ዘላቂ ሕይወቱንም ሆነ ሌሎችን አነደሚነካ ማሰብና ለውሳኔው ሃላፊነት መውሰድን ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: አሁን ላይ የሚደረጉ ውሳኔዎች  የወደፊት ሕይወት ዕድሎችን  እንዲሁም በራስ ማንነት እድገትና በሌሎች ሰዎች ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖዎች ይታያሉ።ሌላው መመርያው የሚዳስሳቸው ጉዳዮች በሃሳብ የመፅናት ክህሎት፣ ግላዊ ግጭቶችን መለየት፣ አወንታዊ የአዕምሮ ጤና ተግባራት እና የግጭት አፈታት መንገዶች ናቸው። ውሳኔ አሰጣጥ ከዕድሜ ልክ ትምህርታዊና ሙያዊ እንዲሁም ግለሰባዊ እድገት ጋር በማዛመድ ከፆታ አንጻርም ይታያል። ተማሪዎች አሁን ላይ ማሕበራዊ ድሕረ-ገፆች ላይ የሚለቋቸው ግላዊ መረጃዎች እንዲሁም ምስሎች የወደፊት የሕይወት ግባቸው ለይ ያላቸውን ተፅዕኖ ይመለከታሉ። ግልፅ የሆኑ ወሲባዊ ንግግሮች የሚኖራቸውን ህጋዊ የቅጣት ደረጃዎችም ይብራራሉ።

___ **8.4 ተማሪው ከጓደኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይመለከታል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪው ይህን የሚያከናውነው ስለ ጓደኝነት አይነት እና እንዴት በሕይወት እድገት ደረጃዎች ውስጥ ጓደኝነት እነደሚለወጥ በመለየት ነው። ተማሪው ጤናማ ስለሆኑ እና ጤናማ ስላልሆኑ ግንኙነቶች ይለያል።  ግላዊ እና የሌሎችን ነጻነት እና መታለፍ የሌለባቸውን መስመሮች ማክበራቸውን የሚያረጋግጡ መንገዶች ለተማሪዎቹ ይተዋወቃሉ።

___ **8.5 ተማሪው በጉረምስና ወቅት ስለሚኖር የፍቅር ግንኙነት ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>:የዚህ መመርያ ይዘት የፍቅርን፣ የአብሮነትንና ማንነትን የማወቅ አስፈላጊነት ላይ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች የፍቅርንና የጊዜያዊ መሳሳብን ልዩነት እንዲያውቁና ከእያንዳንዱ ግንኙነት

ስለራሳቸው የሚማሩት ነገር እንደሚኖርና እነዚህ ልምዶችም ለትዳር ሕይወት ሃላፊነቶች የሚያዘጋጁ ፈተናዎች እነደሆኑ ይመረምራሉ። ከዚህ በላይም ተማሪዎች ጎጂ የሆኑና አሉታዊ አዕምሮአዊ ተፅዕኖ ያላቸውን የፍቅር ግንኙነቶች መለየት ይችላሉ።

___ **8.6 ተማሪው ስነ ወሲብን የተመለከቱ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ መልክቶችን ይለያል።**

<u>መግለጫ</u>: ተማሪወች ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ማስታወቂያዎችን፣ ሙዚቃዎችንና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን፣ ፊልሞችን የታተሙውጤቶችን እና፣ በየግድግዳው ያሉ ፅሁፎችንና ስዕሎችን ለይተው ማወቃቸውን ይቀጥላሉ። በዚህም እነዚህ መልዕክቶች በራሳቸውም በሌሎችም ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ይመረምራሉ፤ የራሳቸውን ግምገማ ካደረጉ በሁዋላ ያገኙት አሉታዊ ተፅዕኖ ላይ ምላሽ እንዲሰጡና ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ እንዴት መንገር እንዳለባቸው ይረዳሉ። በመገናኛ ብዙሃን ከመዘፈቅ ይልቅ ሌሎች አማራጮች ይታያሉ። ተማሪዎች እነዚህ መልዕክቶች እንዴት አዕምሮአዊ ጤና ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩና አጥቂዎች እንዴት ተጠቂዎችን ለመሳብ እነደሚጠቀሙበት ያሳያሉ።

___ **8.7 ተማሪው ከ ጋብቻ በፊት ለሚደረጉ ወሲባዊ ግንኙነቶች 'አይሆነም' ለማለት የሚያገዙ መንገዶችን ያብራራል።**

<u>መግለጫ</u>: የዚህ ትኩረት የሚሆነው በራስ መተማመን ችሎታ፣ በሃሳብ የመፅናት ክህሎት እና የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶች ላይ ነው። ተማሪዎች የራሳቸውንም ስሜት እና የአቻ ግፊትን ተቋቁመው ከ ጋብቻ በፊት ለሚደረግ ወሲባዊ ግንኙነት ለምን እና እንዴት 'አይሆነም' ማለት እነዳለባቸው ይማራሉ።

___ **8.8 ተማሪው ጭንቀትን እነዴት ማሰተናገድ እንዳለበት ክህሎቶችን ያዳብራል።**

<u>መግለጫ</u>: ተማሪዎች ለጭንቀት ምንጭ የሚሆኑ ምክንያቶችን(ቤተሰባዊ፣ የአቻ፣ የትምህርት ቤት፣ የአፍላ ዕድሜ እርግዝና እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ. ስጋት) ይለያሉ፤ እንዲሁም እነዚን ጭንቀቶች ማስተናግጃ አወንታዊና አሉታዊ መንገዶችን ይለያሉ። ዋናው ነገር ጭንቀት ሁሌም ሊኖር የሚችል ነገር ሲሆን ሁሌም አሉታዊ ነው ማለት ግን አይደለም። እነደ አልኮል፣ ንጥረ ነገሮች እንዲሁም ራስን ማጥፋትን የመሳሰሉ አሉታዊ የሆኑ ጭነቀትን የማስተናገጃ መነገዶችን ለመቅረፍ መረጃዎች ይቀርባሉ። ተማሪዎች አወንታዊ የሆኑ አካላዊና አዕምሮአዊ ጭንቀትን ማስተናገጃ መንገዶች ይማራሉ። ለምሳሌ:- ስፖረታዊ እንቅስቃሴዎች፣ የፈጠራ ስራዎች፣ ሐይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች፣የወጣት ማሕበራት፣ ሙያዊ ና የማንነት መገንቢያ እንቅስቃሴዎች ይጠቀሳሉ።

___ **8.9 ተማሪው በቤት ፣በትምህርት ቤት እንዲሁም በማሕበረሰብ ዉሰጥ በተከሰተ ለውጥ ምክንያት የሚመጣ ጭንቀትን ይለያል።**

<u>መግለጫ</u>: ይህ ትኩረት የሚሰጠው ከህመም፣ የአካል ጉዳት ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች፣ ሞት፣ መለያየት፣ ፍቺ፣ ጓደኛን ማጣት፣ የገቢ ምንጭን ማጣት ወይም ከሱስ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ሃዘኖች እና የለውጦች ሒደት ላይ ነው። ዋናው ነጥብ ለውጦች ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችን እና አዳዲስ ጓደኝነቶችን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ። በተጨማሪም ደግሞ በተለይ በጉረምስና ወቀት ያሉ ጓደኝነቶች መደበኛ ጭንቀት ሲኖራቸው እነዚህ ጭንቀቶችም ጊዜያዊ ናቸው። ተማሪው አወንታዊ አዕምሮአዊ ተግባራትን ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቀምባቸዋል።

___ **8.10 ተማሪው ከአፍላ እድሜ እርግዝና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይተነትናል።**

<u>መግለጫ</u>: በዚህ ውስጥ የአፍላ እርግዝና አካላዊ፣ ማሕበራዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ህጋዊ፣ ትምሕርታዊ፣ ስነልበናዊ እና ስነ ምግባዊ አንደምታዎች ይቃኛሉ።

___ **8.11 ተማሪው የአልኮል እና ሌሎች ንጥረ ነገሮች ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም በቤተሰብ እና በ አቻ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ያብራራል።**

መግለጫ: የንጥረ ነገሮች ያልተገባ አጠቃቀም በ አቻ ቡድን ዉስጥ የሚኖረው ማሕበራዊና ስነ-ፆታዊ ተፅዕኖ ይቃኛል። በቤተሰብ ዉሰጥም የሚኖር ይህ ያልተገባ የንጥረ ነገር አጠቃቀም ከቤተሰባዊነትና ከፆታዊ ጥቃት አንፃር ይታያል።

___ **8.12 ተማሪው ስለ ጾታዊ ጥቃት፣ መደፈር(በፍቅር አጋርም ጨምሮ)፣ በስጋ ዘመዶች መሀል ስለሚፈጸም ወሲብ፣ወሲባዊ ማባበል፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ስላለው ተጽዕኖና ስለመከላከያ መንገዶቹ ይተረጉማሉ**

መግለጫ: ይህ ስለ ክርክር ችሎታ፣ ግጭት አፈታት፣ አስጊ ሁኔታዎችን ስለመከላከል እና አይሆንም ስለማለት ይተነትናል። አካላዊ እና አዕምሮዊ ጎጂ የሆኑ ግንኙነቶች እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ስለሆኑ ጥቃቶች መገለጫዎች ይብራራል። ስለጥቆማ እና ህጋዊ አንደምታዎችም መረጃዎች ተካተዋል። በተጨማሪም አጥቂዎችን በመለየት ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂነትን ስለመለየት፣ የዝውውሩን አይነት ስለመረዳት እነዲሁም እንዴት የማይጎዳና ሀላፊነት የተሞላበት የሕይወት ውሳኔበመወሰን ራሳቸውን ከህገወጥ ዝውውር መጠበቅ እንደሚችሉ ይረዳሉ።

___ **8.13 ተማሪው የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ያስታውሳል።**

መግለጫ: ይህ የሚያካትተው ለቫይረሱ አጋላጭ የሆኑ ባህርያት ምንነት፤ ስለቫይረሱ መተላለፊያ መንገዶች የሚነገሩ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማጥራት እና ለቫይረሱ አጋላጭ ከሆኑ ባህርይዎች ስለመታቀብ ነው። ቫይረሱን ለመከላከልም ኮንዶምን ስለመጠቀም ይብራራል።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________